ספריית פיג'מה לקטנטנים

**በአንድ ወቅት ብቻውን መተኛት የማይፈልግ ልጅ ነበር**

**ለቤተሰባዊ ተሳትፎ የሚመከሩ**

**የሕፃኑ ወደ ሌሊት መግባት በአንጻሩ ለጉዞ እንደመውጣት ነው፤ ሁል ጊዜም የነገርኩት ታሪክ ወደዚህ ጉዞ ሲጀምር ትንሽ እንደሚሸኘው ተስፋ አደርጋለሁ፤ ይህም ጉንጩ ላይ እንደ መሳም ዓይነት በመንገድ ላይ ከእርሱ ጋር የሚወስደው እንደ አስደሳችና የተጠበቀ ትዝታ ይሆናል።**

[ዳቪድ ግሮስማን፣ "ብቶኽ በዓት ሲፑር ሃዔሬቭ"፣ 7 ቀናት፣ ዪዲዖት አሕሮኖት]

**ለቤተሰባዊ ንባብ ጠቃሚ ምክር**

አብረው ማንበብ ታዳጊ ሕጻናትን የመጽሐፉን ጀግና እንዲያውቁ ያስችላቸዋል። ከወላጆች ጋር አንድ ላይ ሆነው ለሚያጨናንቋቸው ስሜቶች ስም መስጠትና ለፈታኝ ሁኔታዎች መፍትሔዎችን ማወቅ ይማራሉ።

**ሚራ ሜኢር** (1932-2016) - የልጆች ደራሲ፣ ገጣሚ፣ ተርጓሚና አርታኢ። 'የኦሬን ኤሊ'፣ 'ሽሉሊ'፣ 'መሳል እወዳለሁ'ን ጨምሮ የልጆች መጻሕፎችን እውቅናና የአንባቢዎችን ፍቅር አሸንፈዋል። ሜኢር የዝዔቭ ሽልማትን ለሕይወት ዘመን ስኬትና ሌሎች ሽልማቶችን አሸንፋለች።

**አሎና ፍራንኬል** [1937] - የልጆች ሰዓሊና ደራሲ። በተለያዩ ቋንቋዎች የተተረጎሙ ከሰላሳ በላይ የህፃናት መጻሕፎችን የጻፈች ሲሆን ከእነርሱም መካከል 'የበርበሬዎች መጽሐፍ'፣ 'የድስቶች ድስት'ና የናፍታሊ ተከታታይ መጽሃፍ ይገኙበታል። በተጨማሪም በሌሎች ደራሲያን የተፃፉ ከአርባ በላይ የሚሆኑ የሕጻናት መጻሕፍትን ስዕላዊ መግለጫዎችን ስላለች። ፍራንኬል ለህፃናቱ መጽሃፍ ስዕላዊ ገለጻዎች ሽልማቶችን አሸንፋለች።

**ውይይት - መተኛት**

ከልጆች ጋር ከመተኛትዎ በፊት ምን እንደሚሰሩ አንድ ላይ መወያየት ይችላሉ፦ ብዙውን ጊዜ አንድ ላይ ዘፈን ይዘፍናሉ? ይተቃቀፋሉ? ምናልባት ታሪክ ያነባሉ? - እንዲሁም ታሪኩን እንዲያነቡ ጓደኞችን መጋበዝ ይችላሉ- አሻንጉሊት፣ ቴዲ ድብና ምናልባትም ብርድ ልብስ።

**ታሪኩን ማዳመጥ**

ኮዱን ስካን ያድርጉና ታሪኩን ማዳመጥ ይችላሉ፤ በሚያዳምጡበት ጊዜ መጽሐፉን ማገላበጥ ይችላሉ።

**ድራማ – ታሪክ ከአሻንጉሊቶች ጋር**

የልጆችዎ ተወዳጅ ፀጉር አሻንጉሊቶችና የእንስሳት መጫወቻዎች እንዲሁ የታሪኩ አካል ሊሆኑ ይችላሉ፡- በእያንዳንዱ ጊዜ የተለየ አሻንጉሊት እየጨመሩና እየቀነሱ ታሪኩን አንድ ላይ ይተውኑ።

**ጨዋታ - በብርድ ልብስ ውስጥ ማን ይተኛል?**

ታዳጊው ሕጻን ዓይኖቹን ይዘጋና አሻንጉሊቷን እርስዎ ከብርድ ልብስ በታች ይደብቃሉ። ዓይኖቹን ሲከፍት እርስዎ ወላጆች ስለ እንስሳው ማንነት ፍንጭ ይሰጣሉ፤ ታዳጊው መገመት አለበት። ይጮኻል? ምናልባትም ይዘላል ካሮትስ ይበላል? ሚናዎችን መቀያየርና ታዳጊው እርስዎ በብርድ ልብስ ስር የደበቁትን ማን እንደሆነ እንዲጠቁማችሁ መፍቀድ ይችላሉ?

- የፈጠራ ስራዎች፣ ኮከቦችና መልካም የምሽት ዘፈኖች በፒጃማ ፒንተረስት ቤተ-መጻሕፍት ላይ እየጠበቁዎት ነው።